የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፮ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 11
ADDIS ABABA 25th December, 2008

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፲፬/፪ሺ፩ ዓ.ም

ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመዋ ጋት የወጣውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኮንቬንሽን ፕሮቶኮል ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፫፻፺፬

CONTENTS

**Proclamation No. 614/2008**

The Protocol to the OAU Convention on the Prevention and Combating of Terrorism Ratification Proclamation …..... Page 4394

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፲፬/፪ሺ፩

## ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመዋጋት የወጣውን የአፍሪካ አንድነትድርጅት ኮንቬንሽን ፕሮቶኮል ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የአፍሪካ ሕብረት ሦስተኛ መደበኛ ጉባዔ ፕሮቶኮሉን እ.ኤ.አ. ጁላይ ፰ ቀን ፪ሺ፬ በአዲስ አበባ ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

አገራችን ይህን ፕሮቶኮል ተቀብላ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፳፰ ቀን ፪ሺ፯ የፈረመች በመሆኑ፤

ይህንኑ ፕሮቶኮል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመዋ ጋት የወጣውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኮንቬ ንሽን ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፲፬/፪ሺ፩” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 614/2008.

## PROCLAMATION TO RATIFY THE PROTOCOL TO THE OAU CONVENTION ON THE PREVENTION AND COMBATING OF TERRORISM

**WHEREAS,** the Third Ordinary Session of the Assembly of Heads of States and Governments of the African Union has, at its session held in Addis Ababa on 8 July 2004 adopted the Protocol to the OAU Convention on the Prevention and Combating of Terrorism;

**WHEREAS,** Ethiopia has signed the Protocol on 28 December 2007;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Convention at its session held on 25th day of November, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Protocol to the OAU Convention on the Prevention and Combating of Terrorism Ratification Proclamation No. 614/2008."

**፪. የፕሮቶኮሉ መጽደቅ**

የአፍሪካ ሕብረት እ.ኤ.አ. ጁላይ ፰ ቀን ፪ሺ፬ በአዲስ አበባ ባካሄደው ሦስተኛ መደበኛ የመሪዎች ጉባዔ ያፀደቀው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሽብርተኝነት መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽን ፕሮቶኮል በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫. የፍትህ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የፍትህ ሚኒስቴር ፕሮቶኮሉ በሥራ ላይ እንዲውል ለማስፈጸም አስፈላጊው ሥልጣን ሁሉ በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**2. Ratification of the Protocol**

The Protocol to the OAU Convention on the Prevention and Combating of Terrorism, which was adopted by the African Union at its third ordinary session on 8 July 2004 is hereby ratified;

**3. Power of the Ministry Justice**

The Ministry of Justice is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the charter.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of December, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**